# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

# በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሎች የግል ህክምና አገልግሎት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 134/2015

2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት አገልግሎት በቅርቡ የዋጋ ማሻሻያ ስለተደረገ በተመሳሳይ ሁኔታ የህብረተሰቡን የመክፈል አቅም ባገናዘበ፤ የተቋማትንና የባለሙያዎችን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የግል ህክምና አገልግሎት ዋጋ ክለሳ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የግል ህክምና አገልግሎት አከፋፈል በክፊል ለተወሰኑ የአስተዳደርና የጤና ባለሙያዎች በቁርጥና በመቶኛ የሚከፈል መሆኑ እና ወጥነትና ፍትሃዊነት የጎደለው በመሆኑ፤ የክፍፍል ስርአቱም የባለሙያዎችን ጥረትና ለስራው ያሳቸውን አስተዋጽኦ ያላገናዘበ እንዲሁም በሰራተኛው መሃል የቡድን ስራን ከማጠናከር ይልቅ ተነሳሽነት እንዳይኖር ሲያደርግ የቆየ መሆኑን በመገንዘብና ይህንን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተቋማት የመንግስት ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሎች እንደመሆናቸው መጠን ከአገልግሎቱ መርህ አንጻር መደበኛ የአገልግሎት አሰጣጡን ማወክ የሌለበት ቢሆንም ወጥነት በሌለው መልኩ የተለያዩ ሆስፒታሎች የራሳቸውን የውስጥ አሰራር በመዘርጋት የግል ህክምና መስጫ ሰአትን ከመደበኛዉ አገልግሎት ጋር በሚጣረስ መልኩ እየተገበሩ የነበረበትን ሁኔታ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የግል ህክምና አሰጣጥ የሙያ አወቃቀር ከመደበኛው ጋር ተናባቢ የሆነና ጥራቱን ለማረጋገጥ ለተፈለገው አገልግሎት ሲሳተፉ የሚገባቸው ባለሙያዎችን በሙሉ ያሳተፈ እንዲሁም ተቋሙ በዚህ ረገድ ሲያሟሉ የሚገባቸውን ስታንዳርዶች እንደ መደበኛው አገልግሎት ሁሉ እያሟላ የሚሄድበትን መንገድ መተግበሩን የሚያረጋግጥ አሰራርና አቅጣጫ አብራርቶ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤
የአዲስ አበባ ከተማ ጤና ቢሮ በአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ ድንጋጌ**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሎች የግል ህክምና አገልግሎት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 134/2015" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

1. **"የግል ህክምና አገልግሎት"** ከድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ውጪ ከመደበኛ የህክምና አገልግሎት ጎን

ሰጎን ባለሙያዎች ከስራ ሰዓት ውጪና በበዓላት ቀን በተመጣጣኝ ክፍያ የተመሳሳሸና የተኘቶ ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ አገልግሎት ማለት ነው፤

2. **"የመደበኛ የሕክምና አገልግሎት ክፍል"** ማለት ሆስፒታሉ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለመደበኛ ሕክምና አገልግሎት ተገቢው የጤና ክብካቤ የሚሰጥበት ክፍል ነው፤

3. **"ማኔጅመንት"** ማለት የሆስፒታሉ ማኔጅመንት ነው፤

4. **"የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ"** ማለት ከተለያዩ የሆስፒታሉ ክፍሎች ከተውጣጡ ባለሙያዎች የሚመሰረትና የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን በሆስፒታሉ ውስጥ ለማቋቋም አዋጭነቱን በዝርዝር አጥንቶ የውሣኔ ሀሣብ የሚያቀርብ ቡድን ነው፤

5. **"ድንገተኛ ህክምና"** ማለት የወሊድ አገልግሎትን ጨምሮ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት ቅጽበታዊ እርዳታ የሚያሻው ያልተጠበቀና የከፋ የጤና መታወክ ሲያጋጥም የሚደረግ የህክምና አገልግሎት ነው፤

6. **"የአገልግሎት ጥራት"** ማለት የተገልጋዩን ህብረተሰብ የጤና አገልግሎት ፍላጎትና የተቀመጡ ስታንዳርዶች በተሟላ ደረጃ ተግባረዊ በማድረግ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ነው፤

7. **"ሆስፒታል"** ማለት ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የሆነ ሆስፒታል ነው፤

8. **"ጤና ጣቢያ"** ማለት ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ ክፍለ ከተማ ጤና ጽህፈት ቤት የሆነ ጤና ጣቢያ ነው፤

8. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

## 3. <u>የመመሪያዉ ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ተጠሪነታቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ለሆኑ የመንግስት ሆስፒታሉችና ጤና ጣቢያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## 4. <u>የመመሪያዉ ዓላማዎች</u>

ይህ መመሪያ የሚከተሉትን አላማዎች ለማሳካት ያለመ ነው፡-

1. የጤና ባለሙያዎች በትርፍ ጊዜያቸው ለሚሰጡት አገልግሎት ተጨማሪ ገቢ እያገኙ ጤና ተቋሙ ውስጥ እንዲቆዩ ማበረታታት የስራ ተነሳሽነታቸውን ማሳደግና የሙያተኞችን ፍልሰት ለመቀነስ እንድያስችል ነዉ፤

2. የመክፈል አቅም ያላቸው ተገልጋዮች በምርጫቸው የሚፈልጉትን የህክምና ባለሙያና የአገልግሎት አይነት በሚፈልጉት የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል በሚመቻቸው ቀንና የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ማታ 11፡30 እስከ ጧቱ 12፡30 እንዲያገኙ በማድረግ ተገልጋዮች በሚያገኙት አገልግሎት እንዲረኩ ማስቻል ነው፤

3. ከግል ህክምና አገልግሎት በሚገኘው ተጨማሪ ገቢ በመጠቀም የመደበኛ አገልግሎቶችን ጥራት ለማሻሻል ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች**

5. **የግል ህክምና አግልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች**

1. የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጠው የመደበኛውን አገልግሎት በማያስተጓጉልና በሚያጠናክር መልኩ መሆን አለበት፤

2. ከምግብ፣ ከመኝታ ክፍሎች አገልግሎትና አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚፈጀው ጊዜ በስተቀር በመደበኛውና በግል ህክምና አገልግሎት መካከል የአገልግሎት ጥራት ልዩነት መኖር የለበትም፤

3. የግል ህክምና አገልግሎቱ መቋቋም በመደበኛ ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚሰጠውን የቀጠሮ ጊዜ ለማሳጠር የሚደረገውን ጥረት ማወክ የለበትም፤

4. በመደበኛው የህክምና አገልግሎት ያልተጀመሩ ወይም የማይሰጡ የህክምና አገልግሎቶች በግል ህክምና ክፍሉ መጀመር ወይም መሰጠት የለባቸውም፤

5. የመደበኛ የህክምና አገልግሎትን ለመጠቀም የመጣን ወይም ህክምና እየተከታተለ ያለን ታካሚ በማንኛውም መልኩ የግል ህክምና አገልግሎትን እንዲጠቀም ተፅእኖ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

6. በግል ህክምና አገልግሎት ህክምናውን እየተከታተለ ያለ ታካሚ ወደ መደበኛ ህክምና በበቂ ምክንያት የገንዘብ አቅም፣ የጤና ሁነታ፣ የህክምና ውስብስብነት እና በመሳሰሉት ማዛወር ቢያስፈልግ የግል ህክምና አገልግሎት ኃላፊና የጤና ጣቢያው ወይም የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር በመነጋገር ሲፈጸም ይችላል እና ለጤና መድህን ተጠቃሚ ከሆነ የጤና መድህን መመሪያውን የተከተለ ይሆናል፤

7. በግል ህክምና አገልግሎት ስራ ላይ ያለ ባለሙያ ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ሲፈለግ ያለ ክፍያ የመስራት ግዴታ አለበት::

8. የግል ህክምና አገልግሎት የህክምና የቡድን አሰራር መንፈስን በተከተለ መልኩ የሚሰራ መሆን

ይኖርበታል፤

9. የድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን በግል ህክምና አገልግሎት ክፍል መስጠት የተከለከለ ነው፤

10. በመደበኛ የስራ ሰአት ከሚሰሩ ባለሙያዎች ውጪ በግል ህክምና ላይ መሰራት አይችሉም፤

11. በትምህርት ላይ ያሉ ማለትም የህክምና ትምህርታቸውን የሚያሻሽሉ ሪዚደንት ሀኪሞች፤ የልምምድ ጊዜ ላይ ያሉ ሀኪሞች ወይም ኢንተርንሺፕ እና የትምህርት ዕድል ያገኙ ሙያተኞች ስራውን መስራት አይችሉም:: ሆኖም ግን ተቋሙ የባለሙያ እጥረት ካጋጠመው በማኔጅመንት ውሳኔ መሰረት ሪዚደንት ሀኪሞችን መጠቀም ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር

### 6. የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም

1. ስለግል ህክምና አገልግሎት የማቋቋሚያ ውሳኔ

   የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሲቋቋም የሚችለው በዚህ መመሪያ የተካተቱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የማቋቋሚያ ሀሳብ ሲቀርብ በጤና ጣቢያው ወይም በሆስፒታሉ ማኔጅመንት በሚሰየም የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ የቴክኒክ ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ በሚካሄድ ጥናትና የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ስራ አስኪያጅ በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት ተገምግሞ ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

2. ስለግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ

   የግል ህክምና መስጫ አገልግሎትን በጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ውስጥ የማቋቋም አዋጭነት በዝርዝር አጥንቶ የውሣኔ ሀሣብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው፤ ይህም ኮሚቴ በሆስፒታሉ ማኔጅመንት ይሰየማል፤ የግል ህክምና አግልግሎት ምስረታ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) የሆስፒታሉን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም የግል ህክምና አገልግሎት አዋጭነትን ያጠናል፤

   ለ) ህክምና ክፍል ሲሰጡ የሚችሉ የጤና አገልግሎቶችን ይለያል፤

   ሐ) የሰው ኃይል ጥናት፣ የአሰራር ጥናትና የፋይናንስ ጥናት በማድረግ በወቅቱ የተለዩ ስጋቶችንና ታሳቢዎችን በዝርዝር ይለያል፤

   መ) ከግል ህክምና ክፍል የሚጠበቁ አገልግሎቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል፤

   ሠ) የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ የግል ህክምና አገልግሎቱ ሲጀመር የስራ ጊዜው ያበቃል፤

### 7. መነሻ የሀብት ምንጭ

የግል ህክምና መስጫ አገልግሎት ማቋቋሚያ ካፒታል የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት በሚፈቅደው መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ምንጭ በተገኘ ካፒታል ሲመሰረት ይችላል፡-

1. ተቋሙ በግል ህክምና አገልግሎት በሰበሰበው ገቢ፤
2. ከጤና ጣቢያ ወይም ከሆስፒታሉ መደበኛ የዉስጥ ገቢ ከሚገኝ ከወለድ ነጻ ብድር፤
3. ከመንግስት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ፤ እና
4. እንዳስፈላጊነቱ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ሊቋቋም ይችላል፤
5. የግል ህክምና አገልግሎት ማቋቋሚያ ከጤና ጣቢያ ወይም ከሆስፒታሉ የዉስጥ ገቢ ወይም ከመንግስት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ በብድር የተገኘ ከሆነ የብድሩ የመመለሻ ጊዜ በጤና ጣቢያው ወይም በሆስፒታሉ ማናጅመንት ይወሰናል፡፡

## 8. ስለ ቋሚ ንብረት

ለግል ህክምና አገልግሎት የተቋሙን ቋሚ ንብረት ያለክፍያ መጠቀም ይቻላል፤ ሆኖም ግን የመደበኛውን አገልግሎት የማያስተጓጉል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡

## 9. ስለ አላቂ ንብረቶች

1. የግል ህክምና መስጫ አገልግሎቱን ለመጀመር ሲወሰን የራሱ አላቂ ንብረቶች እንዲኖሩት ይደረጋል፤
2. የግል ህክምና መስጫ ክፍሉ አላቂ ንብረቶችን በራሱ ማዘጋጀት ካልቻለ በተቋሙ እንዲቀርብ ይደረጋል፤
3. የአላቂ ንብረቶች ግዢ በግዥ ዕቅድ መካተቱንና በየወሩ የተቀመጠውን ቁሳቁስ ሂሳብ ለተቋሙ ገቢ እንዲያደርግ የሚያስችል የአሰራር መዘርጋትና ተፈጻሚነቱንም በውስጥ ኦዲት እንዲሁም ማኔጅመንት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 10. የአገልግሎት ቅንጅት እና ስብጥር

1. የግል ህክምና አገልግሎቱ በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሉ እንዲጠቀምበት የተፈቀደለትን መሰረተ ልማት እና የህክምና መሳሪያዎች ያለምንም ወጪ መጠቀም ይችላል፤
2. የስራ ተያያዥነት ያላቸው የመደበኛ አገልግሎት ልዩ ልዩ ክፍሎች ከግል ህክምና አገልግሎት ጋር ተቀናጅተው መስራት አለባቸው፤

## 11. የግል ህክምና አገልግሎት አደረጃጀት

1. የጤና ተቋማት የግል ህክምና አገልግሎት በተመላላሽ ወይም/እና በተኝቶ ህክምና አገልግሎት ሊደራጅ ይችላል::

2. የግል ህክምና የተኝቶ ህክምና አገልግሎት ከመደበኛው የተኝቶ ህክምና አገልግሎት አጠቃላይ አልጋ እስከ 20% መጠቀም ይችላል ነገር ግን ለድንገተኛ አገልግሎት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደበኛ

አገልግሎት ይውሳል፣

3. ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ ለግል ህክምና አገልግሎት ከተመደበው አልጋ ውስጥ በመደበኛ አገልግሎት ባሉት ክፍሎች የሥራ ጫና አንፃር ይከፋፈላል፤

4. ለግል ህክምና አገልግሎት ክፍል የራሱ ኃላፊ እና የሙሉ ጊዜ ጸሐፊ ወይም ሪሴፕሽኒስት በጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ይመድባል፤ የሰራተኞቹ የደመወዝ አከፋፈል በመንግስት የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት ሆኖ ተጨማሪ እንደ አገልግሎቱ መጠን የማትጊያ ክፍያ በፐርሰንት ይከፈላቸዋል፤ የግል ህክምና ክፍሉ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ሆኖ የማኔጅመንት ኮሚቴ አባል ሲሆን በቀጥታ የህሙማን ህክምና አገልግሎት ላይ አይሳተፍም፡፡

12. <u>የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል አስተዳደር</u>

1. በግል ህክምና አገልግሎት የሰራተኞች አመዳደብ በጤና ጣብያው ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት ይሆናል፤
2. በመደበኛ አገልግሎት አሰጣጥ በእውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በተነሳሽነታቸው፣ በመደበኛ የሥራ ሰአት ባላቸው የሥራ ውጤትና በሙያ ስነ-ምግባራቸው የተሻሉ እና ፍቃደኝነታቸው እየታየ በግል ህክምና ክፍል ውስጥ በሚወጣው የሥራ ፕሮግራም መሰረት በየተራ እየተመደቡ እንዲሰሩ ያደርጋል፤

3. አንድ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት ሰዓት የሚሰጠው አገልግሎት በምጣኔ ሲሰላ በመደበኛ አገልግሎት ከሰጠው ግልጋሎት አንጻር አጠቃላይ በግል ህክምና አገልግሎት ያከናወናቸው ተግባራት ምዘና በየወሩ ሲሰላ የመደበኛውን አገልግሎት ስልሳ በመቶ (60%) መብለጥ የለበትም፤ይህንንም ለማስፈፀም እንዲያስችል የእያንዳንዱ ፈፃሚ ባለሙያ የግል የዕለት ሥራ አፈፃፀም መከታተያ መዝገብ (Log Book) በጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ ይዘጋጅለታል፤

4. በመደበኛ ህክምና ለተኙት ህክምና አገልግሎት የሚመደብ የሰው ኃይል መጠን በምጣኔ ለግል ህክምና አገልግሎት ለተኙት ታካሚዎች መመደብ ይኖርበታል፤

5. ማንኛውም በግል ህክምና አገልግሎት ለመሳተፍ የሚፈልግ የጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ ሰራተኛ፤ ባለሙያ የኮንትራት ውል ከጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ ጋር መፈራረም ይኖርበታል፤

6. በተመሳሳይ ሰዓት በመደበኛ ወይም በተረኝነት ተመድቦ የሚሰራ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት መመደብ የለበትም፤

7. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኃላፊ በውድድር የሚመደብ ይሆናል፤

8. የግል ህክምና አገልግሎቶች ባለሙያ በኮንትራት በመቅጠር መመደብ ቢያስፈልግ በጤና ጣብያ ወይም

ሆስፒታሉ ማኔጅመንት የግል ህክምና ክፍል ግልጽ የማወዳደሪያ መስፈርት ማውጣት ይኖርበታል፤

9. ለግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የጥበቃ፣ የጽዳት፣ ጠቅላላ አገልግሎት፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ ፋይናንስ፣ ግዥ፣ ስምሪት እና የመጋዘን የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ የጤና ጣቢያ ወይም የሆስፒታሉን መደበኛ አገልግሎት በማያስተጓጉል መልኩ መሆን አለበት፤

10. በግል ህክምና ክፍል ውስጥ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ምደባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ በዚሁ ንኡስ አንቀፅ (2) በተጠቀሰው መሰረት በዙርና በየተራ እንዲመደቡ ይደረጋል፤

11. የግል ህክምና አገልግሎት ለሚያከናውናቸው ሥራዎች በመደበኛው አገልግሎት የሚሰሩ ሰራተኞች አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

## 13. <u>የግል ህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት</u>

በግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት፡-

1. ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ሰአት የህክምና አገልግሎቱ ከመደበኛ የስራ ሰአት ከጧቱ 2፡30 እስከ 11፡30 ውጪ የሚሰጥ ይሆናል

2. ለተኝቶ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት

   ሀ) በግል ህክምና ተኝተው ለሚታከሙ ተገልጋዮች የ24 ሰአት ህክምና አገልግሎቶቹ የሚሰጡት በመደበኛ ሰአት ተኝተው ታካሚ ክፍል ውስጥ በተመደቡ ባለሙያዎች ይሆናል፤

   ለ) የቀዶ ጥገና አገልግሎት ሲሰጥ የሚችለው ከመደበኛ የስራ ሰአት ውጪ የሚሰጥ ይሆናል ማለትም ማታ 11፡30 እስከ ጧቱ 2፡30 ድረስ አገልግሎት መስጠት ይቻላል፤

3. በቢህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ —ሀ“ ላይ ላሉ ተገልጋዮች ድንገተኛ የቀዶ ጥገና አገልግሎት ካስፈለገ በማንኛውም ሰአት የሚሰጥ ይሆናል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የተገልጋዮች መብትና ግዴታ</u>

## 14. <u>የተገልጋዮች መብትና ግዴታ</u>

1. የተገልጋዮች መብት አጠቃላይ የጤና ጣቢያ ወይም የሆስፒታል ተገልጋይ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ተገልጋዮች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡-

   ሀ) በተቻለ አቅም አጭርና የተመቻቸ የህክምና ቀጠሮ ማግኘት

ለ) ተገልጋዩ በፈለገው ባለሙያ የመታከም

ሐ) ተገልጋዩ አገልግሎት ጨርሰው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በተመሳሳይ ህመም በተመሳሳይ ባለሙያ ለተከታታይ 15 (አስራ አምስት) ቀናት ያለተጨማሪ የካርድ ክፍያ የህክምና አገልግሎቱን የማግኘት መብት አለው፤

መ) በግል የህክምና አገልግሎት የሚሰጠውን የአገልግሎት ዝርዝር፤ ዋጋ እና የባለሙያዎችን ስም፣ የሙያ ደረጃ እና ስያሜ የማወቅ መብት አለው፤

ሠ) ለታከመው ህክምና በፅሁፍ የሀኪም ማስረጃ የማግኘት መብት አለው

2. የተገልጋዮች ግዴታ

ሀ) የጤና ጣቢያ ወይም የሆስፒታሉን የመደበኛውን እና የግል የህክምና አገልግሎት ህግና ደንብ ማክበር

ለ) የህክምና ስነምግባርን ከሚጋፉ ድርጊቶች መቆጠብ፤

ሐ) ለግል የህክምና አገልግሎት የተተመነውን ቅድመ ክፍያ መፈጸምና አገልግሎቱን ሲጨርስ ሂሳቡን የማወራረድ መብት አለው፡፡

## 15. <u>የተቋሙ ግዴታዎች</u>

1. በግል ህክምና የሚሰጠው አገልግሎት በመደበኛውም አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ማሳወቅ፤

2. የአገልግሎት አቅርቦት እንደ ምግብ፣ አልጋና ሌሎች አገልግሎቶች የማቅረብ፤

3. በመደበኛውም ሆነ በግል ህክምናው የሚሰጠው አገልግሎት በጥራት ተመሳሳይ መሆኑን ማሳወቅ፤

4. ሁሉንም አይነት የአገልግሎት ዋጋ ተመን ግልጽ በሆነ ቦታ መለጠፍ፤

5. ሀኪሞች ሙሉ ስማቸውን፣ የሙያ አይነትና አገልግሎት የሚሰጡበትን ቀን በግልጽ መለጠፍ፤

6. አገልግሎቱ በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሉ በመደበኛው አገልግሎት እስካልተሰጠ ድረስ በግል ህክምና ክፍሉ እንዳይሰጥ ማድረግ፤

7. በግል ህክምናው ተመድበው በመስራት ላይ ያሉ የጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ ሰራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች ስራ ሲያስተጓጉሉ የመደበኛውን ስራ እንደበደሉ ተቆጥሮ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ መውሰድ፤

8. አገልግሎቱ በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ሰዓት ብቻ መሰጠቱን ማረጋገጥ፤

ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ የዋጋ ተመን፣ የገቢ ክፍፍል፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና ኦዲት

### 16. የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የዋጋ ተመን

በግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ታካሚው ለተሰጠው አገልግሎት የሚከፍለው የክፍያ ታሪፍ በታካሚው ላይ ከፍተኛ ጫና በማይፈጥርና ለባለሙያዎች ተመጣጣኝ ገቢ በሚያስገኝ አግባብ ሆኖ ከተዘጋጀው የአገልግሎት ክፍያ ጣሪያ መብለጥ የለበትም፤

### 17. የገቢ ክፍፍል

1. ከጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ጠቅላላ ገቢ ላይ የአላቂ መገልገያ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ከአገልግሎቱ የተገኘ ትርፍ እንደሆነ ይቆጠራል፤ ከተጣራው የግል ህክምና ገቢ 10% ለሆስፒታል፣ 15% ለአስተዳዳር ሰራተኞች እና ቀሪው 75% ለባለሙያዎች የሚከፋፈል ይሆናል፡፡ ከሁሉም እኩል 1 አንድ በመቶ ተቀንሶ 3% የግል ህክምና ክፍል ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፤

2. የባለሙያዎቹ ድርሻ የሆነው 74% የትምህርት ደረጃ፣ በሥራው ላይ ያለው ተፈላጊነትና ያሳለፈውን የሥራ ሰዓት ባገናዘበ መልኩ በተቀመጠው የገቢ ክፍፍል ቀመር መሰረት ሥራ ላይ ይውላል፤

3. ለአስተዳደርና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ድርሻ ከሆነው 14% ውስጥ በሥራው ላይ ያለው ተፈላጊነትና ያሳለፈውን የሥራ ሰዓት ባገናዘበ መልኩ በተቀመጠው የገቢ ክፍፍል ቀመር መሰረት ሥራ ላይ ይውላል፤

4. በግል ህክምና አገልግሎት ስም ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀመጠው 3% ገቢ የግል ህክምና አገልግሎቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ገንዘቡን ለመጠቀም እቅድ ሲያቀርብና የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት ሲያፀድቀው ገንዘቡ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፤

5. ከግል ህክምና አገልግሎት የሚገኘው 9% የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ድርሻ በጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት ውሣኔ ሁለንተናዊ የጤና ጣቢያውን/የሆስፒታሉን አገልግሎት ጥራት ለሚያሻሽሉ ተግባራት የሚውል ይሆናል፤

6. ከላቦራቶሪ እና ዲያግኖስቲክስ እንዲሁም ተያያዥ ምርመራዎች አገልግሎት የሚገኝ ትርፍ የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ ባለሙያዎች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ወደ ቸል ገብቶ የሚከፋፈል ሲሆን ማንኛውም ሀኪም ካዘዘው የላቦራቶሪ ወይም የዲያግኖስቲክስ ምርመራ አገልግሎት ክፍያ በቀጥታ ገቢ ሲያገኝ አይገባም፤

7. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 16 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት የገቢ ክፍፍል ቀመር ሲያፀድቅ በዚህ መመሪያ አባሪ የተደረገውን የግል ህክምና አገልግሎት የትርፍ ክፍፍል መነሻ በማድረግ ይሆናል፤

8. ከሌሎች ተቋማት የተላኩ ምርመራዎች ባገለገሉት ክፍል የሚስተናገዱ ሲሆን አፈጻጸሙም መደበኛ የግል ህክምና ክፍፍል አሰራርን ተከትሎ ይሆናል፡፡

**18.** **<u>የፋይናንስ አስተዳደር</u>**

የገቢ አሰባሰብና ክፍያ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ለግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤ግዥዎችና የንብረት አስተዳደር ሥራዎች የመንግስት የፋይናንስ መመርያን የተከተሉ መሆን አለባቸዉ፤

2. የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል የሚሰበስበዉ ገቢ በጤና ጣቢያ /በሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ምዝገባና ፈቃድ በሚታተም ደረሰኝ ይሆናል፤

3. የሚሰበሰበዉ ገቢ ለየግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት እንዲዉል በሚከፈት ልዩ የባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ይደረጋል፤

4. ገቢዉ ለዚሁ አገልግሎት በሚመደቡ የዕለት ገቢ ሰብሳቢዎች አማካኝነት የሚሰበሰብ ሲሆን ወደ ባንክ ገቢ እስኪሆን ድረስ በአስተማማኝ ካዝና እንዲቀመጥ ይደረጋል፤

**19.** **<u>የባንክ ሂሳብ ስለማንቀሳቀስ</u>**

1. በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊና በጤና ጣቢያ /በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ጣምራ ፊርማ ወይም

2. የጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ በሌለ ጊዜ በጤና ጣቢያ /በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊ እና ለጤና ጣቢያ በጤና ጣቢያው ሜዲካል ዳሬክተር እንዲሁም በሆስፒታል የሆስፒታሉ ምክትል ስራ አስኪያጅ አስተዳዳር እና ቢዝነስ ልማት ዘርፍ ይሆናል፡፡

## 20. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች

1. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች ጤና ጣቢያው/ሆስፒታሉ የሚሰጣቸዉ

   ሀ) የተመላላሽና የተኝቶ ህክምና አገልገሎት፤

   ለ) የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ አገልግሎቶች፤

   ሐ) የምግብ እና የመኝታ አገልግሎት፤

   መ) የጤና ምርመራ ማስረጃ አገልግሎት እና

   ሠ) ሌሎች በግል ህክምና የሚሰጡ ተጓዳኝ የህክምና አገልግሎቶች ይሆናሉ፤

2. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢ ከመድኃኒትና ከአላቂ የህክምና መገልገያ እቃዎች ሽያጭ የሚገኝን ገቢ አያጠቃልልም፤

3. ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸዉ የግል ህክምና አገልግሎቶች የሚገኘዉ ገቢ ለክፍያ አፈጻጸምና በግልጽ ለሚቀርብ የፋይናስ ሪፖርት አጋዥ ይሆን ዘንድ ለየገቢ ምንጩ ኮድ እንዲኖረዉ ይደረጋል፤

4. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረስ ስምምነት መሰረት የዱቤ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

## 21. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ

1. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የራሱ የሆነ የሂሳብ መዝገብ፤ የባንክ ሂሳብ፤ የገቢ ደረሰኝና ልዩ ልዩ ቅጻቅጾች ከመደበኛዉ ሂሳብ ተለይተዉ ይኖሩታል፤

2. ማንኛዉም የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢና ወጪ በየዕለቱ መመዝገብ አለበት፤

3. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚጠቀምባቸዉ የሂሳብ ሰነድ ዓይነቶች ይዘት በመደበኛዉ አገልግሎት ሥራ ላይ የሚዉሉት አይነት ይሆናሉ፤

4. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢና ወጪዎች በሂሳብ መዝገብ በአግባቡ ተመዝግቦ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፤

5. የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሂሳብ አያያዝ የሀገሪቱን የሂሳብ አያያዝ አዋጅ፡ ደንብና

መመሪያ ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

## 22. <u>የኦዲት አገልግሎት</u>

1. የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ የዉስጥ ኦዲተር ስለ የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎትና የሂሳብ አያያዝ ለጤና ጣቢያ ወይም ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ክትትል በማድረግ ያማክራል፤ ሪፖርት ያቀርባል፤
2. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ ቢያንስ በሩብ አመት አንድ ጊዜ በዉስጥ ኦዲተር ይመረመራል፤
3. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በዉጭ ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፤
4. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ የሚመረመረዉ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ይሆናል፤

## 23. <u>የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ</u>

1. የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት ሂሳብ በየወሩ፤ በሩብ አመት እና በአመት ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅና ለሌሎች ለሚመለከታቸዉ አካላት በወቅቱ መቅረብ አለበት፤
2. የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የመንግስት የፋይናንስ ቢሮ በሚያሳትማቸው የሂሳብ ማቅረቢያ ፎርሞችን በመጠቀም፤

   ሀ) የገቢ ሪፖርት

   ለ) የወጪ ሪፖርት

   ሐ) የተሰብሳቢ ሪፖርት

   መ) የተከፋይ ሪፖርት

   ሠ) የሂሳብ ሚዛን

   ረ) የሳጥን ሂሳብ ሪፖርት

   ሰ) የባንክ ማስታረቂያ

   ሸ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ወዘ ሪፖርት መቅረብ አለበት፤

የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት አጠቃላይ አመታዊ ሪፖርት ለጤና ጣቢያ/ለሆስፒታሉ ማኔጅመንት ቀርቦ መገምገምና መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ተግባር፣ ኃላፊነት እና ክትትልና ግምገማ

### 24. የቢር ተግባርና ኃላፊነት

1. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
2. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዳል፤የአሰራር ማሻሻያ ያደርጋል፣
3. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ መልካም ተሞክሮችን ይቀምራል፣ ያሰፋል፤
4. ለግል ሕክምና አገልግሎት ማጠናከሪያ የሚሆን ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፤
5. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ መከታተያና መገምገሚያ መስፈርት ያወጣል አሰራሩን ለማጠናከር የሚያስችል የድጋፋዊ ክትትል ስርዓት ይዘረጋል፤
6. ስለግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ የሚቀርብለትን የአፈፃፀም ሪፖርቶች ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

### 25. የጤና ጣቢያው ቦርድ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት

1. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም በቀረበው ሰነድ ላይ ተወያይቶ ክፍሉ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ውሳኔ ያስተላልፋል፤
2. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ተግባር በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን በተመለከተ የሚከናወኑ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በበላይነት ይደግፋል፣፤
4. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ ምደባ በውድድር ሆኖ በሆስፒታሉ ማኔጅመንት ውሳኔ የሚወሰን ይሆናል፤
5. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን የመነሻ ካፒታል መጠንና ምንጭ ይወስናል፤
6. በዚህ መመሪያ የወጣውን የክፍያ ማዕቀፍ መሰረት አድርጎ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል የአገልግሎት ክፍያ ተመን መፈጸሙን ይከታተላል፤
7. የግል ህክምና አገልግሎትን የገቢ ክፍፍል ቀመር ያስፈጽማል፤ ይከታተላል፤

8. የግል ሕክምና አገልግሎት አስተዋፅኦና የአገልግሎት አሰጣጡ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ይገመግማል፤ ይከታተላል፤

9. የግል ሕክምና ክፍሉን አስመልክቶ የቀረበውን የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ አመትና አመታዊ ሪፖርቶችን ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፤

10. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን አመታዊ እቅድና በጀት ገምግሞ ያፀድቃል፤

11. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፤

## 26. <u>የጤና ጣብያ ወይም ሆስፒታሉሥራ አስኪያጅ</u>

1. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለመቋቋም የሚያስችል ጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ከማኔጅመንቱ ጋር በመሆን ይመርጣል፤ ይሰይማል፤

2. በጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ተጠንቶ የቀረበውን ጥናት ገምግሞ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት አቅርቦ ያስወስናል፤

3. የወጣውን መስፈርት መነሻ በማድረግ ማኔጅመንቱን ባሳተፈ ሁኔታ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ በመምረጥ ለጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ማኔጅመንት አቅርቦ ያፀድቃል፤

4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ያለውን ሥራ ለማከናወን የሚያግዙ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

5. የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን ለማስጀመር፣ ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን ሀብት ያፈላልጋል፤

6. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ለመከታተል የሚያስችል ቼክሊስት ያዘጋጃል፣ በዚሁ መሰረት ክትትል ያደርጋል የማሻሻያና የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

7. የግል ሕክምና አገልግሎት ከመደበኛ አገልግሎት ጋር የተቀናጀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

8. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ በየወቅቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት ገምግሞ ለሆስፒታሉ ማኔጅመንት ያቀርባል፤

9. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያስተባብራል፤

10. በግል መስጫ ክፍሉ ውስጥ ስለሚሰጠው የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበል በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላሉ፤ ይገመግማሉ፤ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

11. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፤ ለሆስፒታሉ ማኔጅመንት ያቀርባል፤

12. በሆስፒታሉ ማኔጅመንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

27. <u>የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ</u>

1. በግል ህክምና አገልግሎት ውስጥ የሚከናወኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፣ አግባብ ያለው የሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተግባር መፈፀሙን ያረጋግጣል፤በሂሳብ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ የቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ገምግሞ ለጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፤

2. የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበልን በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላል፣ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረጉ የተተመኑ ወይም የተከለሱ የአገልግሎት ክፍያዎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን እና መታውቃቸን ይከታተላል፤

4. በየጊዜው ክትትል በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ሙስና፣ ብክነትና ምዝበራ እንዳይፈጠር ቁጥጥር ያደርጋል፤

5. በግል የሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሰራተኞችን ይመድባል፣ የተመደቡ ሰራተኞችን ዝርዝር በግልፅ ቦታ በመለጠፍ ሰራተኞች እንዲያውቁት ያደርጋል፣ ሰራተኞች በምድብ ቦታቸው ተገኝተው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በወሩ መጨረሻም አስፈላጊውን መረጃ ለሂሳብ ክፍል ያስታውቃል፤

6. በግል የህክምና መስጫ ክፍል ከሚሰጡ አገልግሎቶች የሚሰበሰቡ ገቢዎችና የሚፈፀሙ ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሠረት መከናወናቸውን በመከታተል ለማኔጅመንት ኮሚቴና ለጤና ጣቢያ/ለሆስፒታሉ ማኔጅመንት እንዲቀርብ ያደርጋል፤

7. መደበኛና ድንገተኛ ኦዲት በባለሙያዎች በማካሄድ የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጡ የታለመውን አላማ ያሳካ ስለመሆኑ ይገመግማል፤

8. በግል የህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሚሠጡ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሥራ ውል እንዲፈራረሙ በማድረግ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ ስለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያከናውናል፤

10. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት በመደበኛ የህክምና ክፍሉ ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣ ተመሳሳይነቱንም ይከታተላል፣ ልዩነት ሲፈጠር የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

11. ለግል ሕክምና ክፍሉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በመለየት ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄ ያቀርባል፣ የተጠየቁት ግብአቶች ተሟልተው መቅረባቸውን ይከታተላል፤

12. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ አዳዲስ የሕክምና አገልግሎቶችን ለማስጀመር ጥያቄ ሲቀርብ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማማከር አዳዲስ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ የውሳኔ ሀሳብ ለሥራ አስኪያጁ ያቀርባል፤

13. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ወርሃዊ የሩብ ዓመትና አመታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለጤና ጣቢያ ወይም ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፤

14. በየሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**28. <u>የግል ህክምና ክፍል ረዳት አስተባባሪ</u>**

1. ኃላፊውን በማገዝ ስራዎችን ያስተባብራል፤
2. ኃላፊው በማይገኝ ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

**29. <u>ክትትልና ግምገማ</u>**

1. የግል ህክምና አገልግሎት አሠራር እና ጥራት ላይ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረጋል፤

2. በክትትል እና ግምገማ ሥራውም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራሉ፤

3. ግምገማ እና ክትትል የሚያስፈልጉ የመረጃ ምንጮች በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሉ ከሚገኝ መረጃና በHMIS ከሚጠናቀር ሪፖርት ይሆናል፤

4. ክትትልና ግምገማ በተዘጋጀ ቼክሊስት እና በተመረጡ አመላካቾች የወር፣ የሩብ አመት፣ የግማሽ አመት እና የአመት ሪፖርት በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፤ በተዋረድም ሪፖርቱን

በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጣል ድጋፋዊ ክትትልም በየጊዜው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**30. ስለተጠያቂነት**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**31. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ቢሮው ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሻል ይችላል፡፡

**32. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች**

1. በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት አሰራርና የአደረጃጀት መመርያ ቁጥር 02/2007 በዚህ መመርያ ተሽሯል፤
2. ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተደነገጉትን ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**33. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**ዮሐንስ ጫላ (ዶ/ር)**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**ጤና ቢሮ ኃላፊ**